የወያኔ ቡድን በህዝብ ላይ ሲሰራ የቆየውን ግድያና በደል መልኩን እና ዘዴውን እየቀያየረ አሁንም በበለጠ የግፍ ተግባሩን ለማከናወን እንቅስቃሴ ላይ መሆኑ ታወቀ ። በቅርቡ የተለያዩ ህጎችን በማውጣት የዜጎችን ሰብዓዊ መብት ከማፈንም በላይ ያሻውን ለመፈጸም እንዲያመቸው እንደ ተራ ነገር አርቅቆ በተንቀሳቃሽ ሮቦቶቹና « ነገ ምን ችግር ያመጣል?» የሚል አዙሮ ማሰቢያ ህሊና ያልፈጠረባቸው የወያኔ በረት ፓርላማ አባለት አማካኝነት አስጸድቆ የአፈና አገዛዙን እጅግ በተጠናከረ መልኩ መቀጠሉ ታውቆዋል ።

በተለይ ማክሰኞ እለት ሰኔ 30 ቀን 2001 ዓ.ም. የምክር ቤቱ አባላት የስራ ዘመን ማብቂያ እለት መሆኑ እየታወቀ ወያኔን በሚመቸው መልኩ ዜጎችን በግልጽ በመግደል ፤ በማሰር ብሎም በማሰቃየት ያመቸው ዘንድ ያቀረበውን ረቂቅ ህግ በችኮላ እንዲጸድቅ ማድረጉ በእጅጉ አሳፋሪ ነው ሲሉ ሲል ዘገባው ገልጦዋል

የወያኔ ቡድን መሪዎች በኢትዮጵያ ህዝብ ደም እጃቸው የተጨማለቀ ነገ አለም አቀፉ ፍርድ ቤት እንደሚቀርቡ ቢያውቁትም በማን አለብኝነት እና በእብሪት ተወጥረው ህዝቡ በሰላም ከእነ ችግሩ እንዳይኖር ለማድረግ እና ለማሰቃየት ሲሉ የጸረ ሽብርተኝነት ህግ የተባለውን የማፈኛ መንገድ እንዲያጸድቅ ማድረጋቸው የሰሞኑ የህዝብ መነጋገሪያ መሆኑ በዘገባው ተመልክቶዋል

በወሬ ወሬ ሰምቻለሁ በሚል ማንኛውም ዜጋ ለእስር ሊዳርግ የሚችልበትን ህግና ዜጎችን ተገደው (ይህ ስየልንም ይጨምራል) ቃል እንዲሰጡ የሚያስገድድ ደንብና ህግ በውስጡ ያጨቀውን የእነመለስ ዜናዊ ረቂቅ ለሆዳቸው ያደሩ ህሊና ቢስ ልበ ድፍን የሆኑ የተወካዮች ምክር ቤት አባላት ነገ መልሶ ራሳቸውን በዚህ ህግ ጠፍንጎ እንደሚጫወትባቸው እያወቁ ለግዜያዊ ጥቅምና ፍርፋሪ ሲሉ ያለ ምንም ማንገራገር እንዲጸድቅ ማድረጋቸው በሃገርና በህዝብ ላይ የሞት ፍርድ እንዲሰጡ ማገናዘብ ያልቻሉ ድውዮች መሆናቸው ታውቆዋል ሲል ዘገባው ጨምሮ ገልጾዋል

መለስ ዜናዊ እስከዛሬ ለ18 ዓመታት በሃገርና በህዝብ ላይ የፈጸመውን ዘግናኝ ወንጀል ለመሸፋፈን ይረዳው ዘንድ በዓለም እስከ ዛሬ ስራ ላይ ያልዋለና ፈጽሞ ወደፊትም ስራ ላይ ሊውል የማይችል ህግ አርቅቆ በተናጋሪ ሮቦቶቹ አማካኝነት ማጽደቁ በህዝብ ላይ መከራና ስቃይ ብሎም የግፍ ቀንበር ለማሸከም ሲል ሰሞኑን ያወጣው አዋጅ አመቺ በመሆኑ ከእንግዲህ ማንኛውም ዜጋ ወያኔን መቃወምም ሆነ ተቃውሞን ማሰብ በሽብርተኛነት ሽፋን ዘብጥያ ከመውረዱም በላይ አሰቃቂ የሆነ ግርፋት እንደሚፈጸምበት የወጣው ህግ ቁልጭ አድርጎ አስቀምጦታል።

የወያኔ ቡድንና መለስ ዜናዊ ባመጡት ጦስ ሃገሪቱና ህዝቡዋ እጅግ አሳሳቢ በሆነ የኑሮ ውድነትና ከአስር ሚሊዮን ህዝብ በላይ ለከፋ ረሃብ ተዳርጎ ባለበት ወቅት ለተራቡ ወገኖች የእርዳታ እህል እንዳይደርስ እየከለከለ ዜጎች በየቀኑ እንደ ቅጠል እየረገፉ ያለውን ሃቅና እውነት የሚያጋልጡትን አንደበት ለመሸበብና ለመቅጣት ይህንን የመሰለ አሳሪ ህግ ማውጣቱ ብዙም አላስገረመም:: ጸረ ህዝቡና አሸባሪው ወያኔ ለ18 ዓመታት ሲፈጽመው የነበረውን ወንጀል የሽፈነ መስሎት ያወጣው ህግ የበለጠ ህዝብን ላመጽ ሚገፋፋ ነው ይላሉ የፖለቲን ታዛቢዎች::

ህዝብን እየገደለ ለቅሶ የሚደርሰው፡ እየሰወረ አብሮ የምያፈላልገው፡ እያስራብ፡ ለርዳታ የመጣውን እያግበሰበሰ የደለበው ወያኔ፡ የሰው ሃይል የለውም እንጂ ቢችል የህዝብን ትሌፎን በሙሉ ከመጥለፍ ወደሁዋላ የማይለው ወያኔ፡ (ኣልሞከረም አይባልም) ያወጣው ጸረ ህዝብ ህግ ብዙዎችን አላስገረመም:: በጸረ ሽብርተኝነት ሽፋን የታወጀው ህግ የዜጎችን መብት ሙሉ በሙሉ የሚያሳጣ ከመሆኑም በላይ ወያኔ ደስ ባለው ግዜ የፈለገውን ዜጋ አስሮ ለማሰቃየት ብሎም እስከ ሞት የሚያደርስበትን ቅጣት ለመወሰን አመቻችቶ በዚሁ ህግ ውስጥ አካትቶ ያጸደቀ መሆኑም ታውቆዋል

ለሆዳቸው እንጂ ለህሊናቸው ያልሆኑ ፤ ነገ ምን ይመጣብኛል ብለው የማያስቡ ሆድ አደር ግለሰቦች የተጠራቀሙበት ፓርላማ ተብዬ የወያኔ በረት በመጨረሻው ሰዓት እጅግ በተጣደፈ ሁኔታ ህጉን ማጽደቃቸው የተጠበቀ ነበር::

ማክሰኞ ሰኔ 30 ቀን ፓርላማው ሊዘጋ በዋዜማው የዜጎችን በሰላም የመኖር መብት በመጣስ የጥቂት ግለሰቦችን መኖር የሚፈቅድ ህግ ሆኖ ሳለ ረቂቁ በችኮላ እንዲጸድቅ ያደረጉት የወያኔ የፓርላማ አባላት ለእረፍት በተመረጡበት የምርጫ አካባቢ ሄደው ከህዝቡ ጋር እንዲገናኙ ይደረጋል ተብሎ አበልና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች እንደሚሰጣቸው ቃል የተገባላቸው ቢሆንም ስብባው ሲጠናቀቅ ያለ አንዳች ክፍያና ውይይት እንዲበተኑ በመደረጉ በጭብጨባ እጃቸው ሲቃጠል የነበሩ የፓርላማ አባላት በንዴት ሲጦፉና ሲቃጠሉ እንደነበር ከስፍራው የመጣው ዘገባ አስረድቱዋል::

የወያኔ የደህንነት መስሪያ ቤት የዜጎችን የሞባይል ፤ የስልክ ፤ፋክስና ኢንተርኔት የመኖሪያ ቤትና የመስሪያ ቤት የመፈተሽ ስልጣን እንዲኖረው የሚፈቅደው አዲሱ ህግ ለፌዴራል ፖሊስም ከመንገድ ላይ አፍኖ ለወራት ማቆየትና ቶርች የማድረግ ስልጣን ያከናነበው መሆኑን ዘገባው ገልጦዋል

ከአዲስ አበባ ጠቅላይ ቤተክህነት እና በተለይ ለአባ ገብረ መድህን ልዩ ጽህፈት ቤት ቅርበት ያላቸውን የታመኑ ውስጥ አዋቂዎችን በመጥቀስ ዘጋቢያችን እንደገለጠው አባ ገብረ መድህንና በአቡነ ሳሙኤል መካከል የተጀመረው ሽኩቻ ይበልጥ የከረረው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ የነብሰ አባት አምስት ጳጳሳትን ከሲኖዶሱ እውቅና ውጪ አስከትለው በጣሊያን አገር ተንሸራሽረው እና የራሳቸውን አጀንዳ አስፈጽመው ከተመለሱ በሁዋላ ነው ብሎዋል

ውስጥ አዋቂዎቹ ባደረሱን መረጃ መሰረት  በ «አባት ነን » ባይ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ሰባኪያን መሃከል የተነሳውን ፍትጊያ አባይ ጸሃዬ ከዚህ ቀደም በሃይማኖት ትንኮሳ ሳቢያ ከተለያዩ የሀናይማኖት መሪዎች ጋር ባደረገው ስብሰባ ልምድ ያለው በመሆኑ ችግሩን እንዲፈታ በመለስ ዜናዊ ትእዛዝ ተሰጥቶት የሲኖዶሱን ስብሰባ እንዲመራ መታዘዙ ታውቆዋል

በታዘዘው መሰረት ስብሰባውን ከመምራቱ አስቀድሞ መለስ ዜናዊን በመተማመን መስቀሉ ቀርቶ ጠብ መንጃ መያዝና ማምለክ የጀመሩት ፤ ከመጽፍ ቅዱሱ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ሰነድ የሚበልጥባቸው አባ ገብረመድህን የሲኖዶሱን ስብሰባ ረግጠው መውጣታቸውንና እሳቸውንም ተከትሎ  ከወያኔ ጋር ሲያስገድሉና ሲያሳስሩ የነበሩ  ሶስት ጳጳሳትም ረግጠው ወጥተዋል

እነሱም አንደኛ»  አባ ገሪማ ፤ሁለተኛ አባ ይስሃቅ ፤ሶስተኛ አባ ዲሚጥሮስ መሆናቸው ሲታወቅ በአባ ገብረመድህን የተደራጁና በቤተክህነቱ የደህንነት መምሪያ ስር የታቀፉና በቢጫ ካርድ የአባልነት መታወቂያ የተሰጣቸው ታጣቂዎች እርስ በእርስ በስለት መሞሻለቃቸውን ለማወቅ ተችሎዋል

በዚሁ 31 ጳጳሳት ባደረጉት ስብሰባ  የአባ ገብረመድህን ጥፋት ቀላል እንዳልሆነና ራሱን የቻለ አንድ ኮሚቴ እንዲቁዋቁዋምና ጉዳዩን አጣርቶ ለሲኖዶሱ ውሳኔ እንዲያቀርብ የተወሰነ ሲሆን በ1989 ዓ.ም. በቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተክርስትያን ውስጥ ህዝበ ክርስትያንን በማስተማር ላይ የነበሩትን አባ ፈቃደ ስላሴን ያስገደሉት አባ ገብረመድህን መሆናቸውን ጳጳሳቱ በይፋ ገልጠው በዚህም ጉዳይ ላይ ሲኖዶሱ እርምጃ እንዲወስድ ጠይቀዋል

ይህን የሲኖዶሱን ስብሰባ የመራው አባይ ጸሃዬ ሲሆን ዓ.ም.የአቡነ ሳሙኤልን የጵጵስና ቆብ አውልቆ ጽጌረዳ አበባ በማስያዝ ግብረ ገብ የጎደለው ስእልና የስም ማጥፋት ላይ ያተኮረ መጽሃፍ ያተሙና ያሰራጩ የአባ ገብረመድህን ተከታዮች መሆናቸው ስለተደረሰበት እንዲያዙና በህግ እንዲጠየቁ አደርጋለሁ» ፓትርያሪኩ በሙስና ተዘፍቀዋል ያላችሁትም በአስቸኩዋይ እንዲጣራ ይደረግ ፤ከስራ የተባረሩ ጳጳሳትም እንዲመለሱ ፤የሚሉ የሲኖዶሱ ስብሰባ መጥራት ያስፈለገበትን ዋና ምክንያት በመደገፍ ነጥብ በነጥብ በማስቀመጥ ሲኖዶሱ ሲሰበሰብ ይህን ውሳኔ ያሳተላልፍ በማለት ትእዛዝ መስጠቱንና ለሰኞ

ሃምሌ ስድስት ቀን 2001 መቀጠሩ ታውቋዋል:: ይህ ደግሞ አብዮታዊ ዲሞክራሲን አምላኪው አባ ገብረመድህንን ኣላስደሰተም::

ይህ በእንዲህ እንዳለ ይህንኑ የጳጳሳት ስብሰባ ለመዘገብ በስፍራው ተገኝቶ የነበረው የአዲስ ነገር ጋዜጣ ዘጋቢ አብርሃም በግዜው በጩቤ ሲሞሻለቁ ከሰነበቱት የአባ ገብረመድህን ጋሻ ጃግሬዎች መካከል ሁለቱ ተከታትለውት ወደ ቢሮው ሲያመራ በሰነዘሩበት ጥቃት መጎዳቱ ተዘገበ:: ጋዜጠኛው በቅዱስ ገብርኤል ሆስፒታል ህክምና የተደረገለት መሆኑ ይታወቅ እንጂ የጤንነቱ ሁኔታ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ለማረጋገጥ አልተቻለም

በቤተክህነት ውስጥ አንድ ተራ ግለሰብ የአባ ገብረ መድህን የቅርብ ዘመድ በመሆኑና በደህንነት ስራ ላይ ተመድቦ የግቢውን ሰራተኞችና ጳጳሳትን ሲያዋክብ የነበረ በስሩም ብዙ ሰላዮችን ያደራጀ ከጥቅማ ጥቅሙ ውጭ በወር 18 ሺህ ብር እየተከፈለው መሆኑን ዘገባው አጋልጡዋል::